# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የኢትዮጵያ ሕብረት ስራ ኮሚሽን

## የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ

## ኦዲት ሪፖርት

የካቲት /2015
አዲስ አበባ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
# የኢትዮጵያ ሕብረት ስራ ኮሚሽን
# የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የኢትዮጵያ ሕብረት ስራ ኮሚሽን የተመደበለትን የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢትዮጵያ ሕብረት ስራ ኮሚሽን ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

**ኦዲታችን፡-**

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶች ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የኢትዮጵያ ሕብረት ስራ ኮሚሽን ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በመ/ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡
የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሕብረት ስራ ኮሚሽን የ2014 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት፤ በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን ጠብቆ የተከናወነ በመሆኑ በእኛ አስተያየት

በባለሥልጣን መ/ቤቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች እና የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓቱ አጥጋቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

## I. <u>ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች (Emphasis of Matters)</u>

1.1 ኮሚሽኑ በአዳማ ከተማ 14ተኛ አለም አቀፍ የሕ/ሥ/ቀንን ለማክበር ባካሄደው ውይይት ላይ ለተሳተፉ 168 ተሳታፊዎች የውሎ የአበል ክፍያ ብር 954,365.00 የተከፈለ ሲሆን ስብሰባው ላይ ለተሳተፉት በባንክ አካውንታቸው ገቢ የተደረገው ዝርዝር ውስጥ ለአንድ ሰው ሁለት ጊዜ በመመዝገባቸው በብልጫ ብር 3,544.00 የተከፈለ መሆኑ ፡-

1.2 ኮሚሽኑ በሂሳብ መደብ 2251101 ብር 376,740.00 ለኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የአየር ጊዜ ኪራይ ክፍያ የፈጸመ ሲሆን ምዝገባው በተፈቀደው የበጀት አርእስት በ2241103 (6253) በማስታወቂያ የሂሳብ መደብ መመዝገብ ሲገባው የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ በ2251101(6271) በስልጠና ሂሳብ መደብ የተመዘገበ መሆኑ፡-

1.3 ለጅማ ዞን ኅብረት ስራ ማህበር እና ለማዕድ ምግብ ማቀነባበሪያ ሕ/ሥራ ማህበር በማስረከባቸው በኮሚሽኑ በአካል ላልተገኙና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) ላልቀረበላቸው ሶስት ተሽከርካሪዎች በ2014 በጀት ዓመት በድምሩ ብር15,286.68 የኢንሹራንስ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፡-

በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

## 2. <u>የሕጋዊነት ጉዳዮች (Compliance Issues)</u>

2.1 መ/ቤቱ ከካድኮ ግሩፕ የንብረትና የንግድ ልማት ኤጀንሲ ኃ/የተ/የግል ማህበር ከመጋቢት 1ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30/2014 የ4 ወር የህንጻ ኪራይ ክፍያ ለመክፈል በተስማሙት መሰረት ብር 4,449,009.60 የከፈለ ሲሆን ግዥው በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም ሲገባው በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ በመሆኑ መንግስት ከውድድር ሊያገኝ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያሳጣው መሆኑ፣

## 3. <u>ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)</u>

3.1 የኮሚሽኑ ሁለት (2) የግዥ ሰራተኞች እና አምስት (5) የጥበቃ ሰራተኞች ለተሰጣቸው ኃላፊነት ዋስትና ወይም ተያዥ ስለማቅረባቸው የሚያሳይ ማስረጃ የሌለ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

### 3.2 <u>የንብረት አስተዳደር</u>

ለኮሚሽኑ የሚገዙ ንብረቶች በፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት በአግባቡ ገቢ እና ወጪ ተሰርቶላቸው ንብረቶቹ በያሉበት ቦታ እንዲሁም በንብረት ክፍል ውስጥ አስፈላጊው ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት በሚያዘው መሰረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ

- ሜክሲኮ ቡናና ሻይ መ/ቤት ቤዝመንት በሚገኝ መጋዘን ውስጥ
    - ☞ የመኪና መለዋወጫ እቃዎች፣ ጎማዎች እና የተለያዩ እቃዎች ተከማችተው የሚገኙ ሲሆን ንብረቶቹ የሚወገዱ እና አገልግሎት የሚሰጡት ተለይቶ ምዝገባ ያልተደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ ለቁጥጥር አመቺ ባልሆነ መንገድ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣
    - ☞ በመጋዘን ውስጥ ያገለገሉ 68 ጎማዎች በኦዲት ወቅት በአካል የተቆጠሩ ሲሆን በንብረት ኮሚቴ በቆጠራ ውጤት መሰረት 79 ጎማዎች የሚያሳይ በመሆኑ በልዩነቱ 11 ጎማዎች በአካል ያልተገኙ መሆኑ፣

- ☞ በበጀት ዓመቱ የንብረት ቆጠራ ቢካሄድም የተቆጠረው በአካል ካለው ንብረት ጋር ተመሳክሮ የንብረት ከወጪ ቀሪ ማመዛዘኛ ያልተሰራ መሆኑ፡-
- ☞ በኮሚሽኑ አስራ አንድ (11) ተሽከርካሪዎች የህይወት ታሪክ የሚያሳይ የግል ማህደር (ማስረጃ) እና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው ያልተገኘላቸው መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

3.3 ባለፉት በጀት ዓመታት የኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት በኮሚሽኑ እርምጃ የተወሰደባቸው መሆኑ ሲጣራ፡-

<u>የ2012 በጀት ዓመት ኦዲት</u>

በአዳማ ከተማ ከክልልና ከፌዴራል ኅብረት ስራ ኤጀንሲ ለተውጣጡ ሰራተኞች በተለያየ ጊዜ ባከናወናቸው የምክክር መድረኮችና ስልጠናዎች ከፌዴራልና ከአዲስ አበባ ለሄዱ ሰራተኞች በብልጫ የተከፈለ ብር 41,672.50 መገኘቱ

<u>በ2013 በጀት ዓመት ኦዲት</u>

የንብረት ቆጠራ ኮሚቴ ቆጠራ ባደረገበት ወቅት ከለቀቁ እና ላፕቶፕ ኮምፒዩተር ያልመለሱ አራት (4) ሰራተኞች መኖራቸው ታውቋል፡፡

**የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት**

**የካቲት 2015 ዓ.ም**